የገቢዎች ሚኒስቴር

Ministry of Revenues

# የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 146/2011

መጋቢት/2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# <u>የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 146/2011</u>

የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንደሚወሰን በህግ የተደነገገ ስለሆነ የገቢዎች ሚኒስቴር በፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀፅ 66 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሚኒስትሩ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 146/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ፡-

   1/ **"የንግድ ሥራ ማቋረጥ"** ማለት በታክስ ከፋይነት ተመዝግቦ የንግድ ሥራ ሲሠራ የነበረና የንግድ ሥራውን ማቆሙን በጽሁፍ ለታክስ ባለስልጣኑ በማስታወቅ ከታክስ ከፋይነት የተሰረዘ ሰው ነው።

   2/ **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ፣ የአዲስ አበባ ገቢዎች ባለሥልጣን እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለሥልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡

   3/ **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

   4/ **"ደንብ"** ማለት የፌደራል ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

   5/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

   ይህ መመሪያ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ባገኘ ታክስ ከፋይ ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

4. **<u>የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ ስለሚገኝ ገቢ</u>**

   ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ሊያገኝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   1/ ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራውን ካቋረጠ በኋላ የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ በእጁ የሚገኙትን ያልተሸጡ ዕቃዎች በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

2/ በንግድ እንቅስቃሴ ወቅት ሊሰበሰብ የማይችል ገቢ ነው ተብሎ የተሰረዘ ገቢ የንግድ ሥራው ከተቋረጠ በኋላ ሲሰበሰብ፣

5. <u>የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ስለሚወሰን ግብር</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት ገቢ ያገኘ ሰው፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኃላ የሚሸጣቸው ዕቃዎች የተሸጡበትን ዋጋ ማረጋገጥ የማይቻል ከሆነ ዕቃው የተገዛበት ዋጋ ወደ ሽያጭ ዋጋ ተቀይሮ ግብሩ ይወሰናል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) (ሀ) የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ዕቃውን የሸጠው የሂሳብ መዝገብ ለሚይዝ ታክስ ከፋይ ከሆነ ዕቃው የተሸጠበት ዋጋ ገዢው በሚያዘጋጀው የግዢ ማረጋገጫ ሰነድ(Purchase Voucher) መሰረት ይወሰናል፡፡

ሐ) የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ የንግድ ዕቃ የሚሸጥ ታክስ ከፋይ የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

መ) ታክስ ከፋዩ ድርጅቱን ሲዘጋ በእጁ ያሉትን ዕቃዎች ቆጥሮ ለታክስ ባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ሠ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ድርጅቱን ከዘጋ በኋላ በሸጣቸው ካፒታል ዕቃዎች ላይ የሚከፈለው ግብር የካፒታል ዕቃዎቹ የመዝገብ ዋጋ(Book value) ከተሸጡበት ዋጋ ላይ ተቀንሶ በሚገኘው ልዩነት ላይ የሚሰላ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ገቢ ያገኘ ሰው የንግድ ትርፍ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለሚከፈለው የንግድ ስራ ገቢ ተፈጻሚ የሚደረገው የትርፍ ህዳግ ግብር ለደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ጥቅም ላይ የሚውለው የትርፍ ህዳግ ይሆናል፡፡

6. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ... ቀን 2011 ዓ.ም.

እዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር
ሚኒስቴር